# እግዚአብሔር በሰነፍ ሰው ዕይታ!

ትላንትና ስለ ዘፋኞቻችን በለጠፍኩ ጽሑፍ ላይ የመሰለውን አስተያየት ለሰጠ ልጅ ጁ ከሰጠው አስተያየት ጋር ፈጽሞ የማይገናኝ ምላሽ (reply) አንዱ የበውቀቱ አድናቂ ይሄንን ከታች የምታነቡትን ለአስተያየቱ ምላሽ (reply) ሰጠው፡፡

Mengst Tigabu ከቲንሺ ሻጀህ ወጣ ብለህ ለመመልከት ሞክር። እስኪ እግረ መንገደን ይህን ጽሁፍ ጋበዝኩህ።

"Bewketu Seyoum

ሕዋዊ ዓለማት እና ሃይማኖት

(በ. ሥ በ Cosmology ጥናት መሠረት የኛዋ መሬት በውቅያኖስ ላይ የተንሳፈፈች የምስር ፍሬን ትመስላለች። የመሬት መጠነ ዙሪያ (circumferance) 40,000 km ሲሆን የገጽታዋ ስፋት (surface area) ደግሞ 510,000,000 sq km ነው። ይዘቷም (volume) 1,000 ቢሊዮን cubic km ነው። ቅርጿን ስፋቷን እና ሌሎች የሂሳብ ስሌቶችን በመጠቀም የመሬት ክብደት 6,000 ቢሊዮን ቶን እንደሆነ ተረጋግጧል። የፀሐይ ክብ የመሬትን 1 ሚሊዮን እጥፍ ይተልቃል። ይህ ማለት ፀሐይ መሀሏ ቀዳዳ ቢሆን ያንን ለመድፈን 1 ሚሊዮን መሬቶች ያስፈልጋሉ ማለት ነው።

ከእኛ ሕዋዊ አካላት (galaxy) የመጨረሻዋ ናት ተብላ የምትታሰበው Pluto ናት። ከፀሐይ እስከ Pluto ያለው ርቀት 6 ቢሊዮን km ነው። ይህ ማለት አንድ አውሮፕላን 1000km/hr ወደ Pluto ቢበር እዚያ የሚደርሰው የዛሬ 700 ዓመት ነው ማለት ነው። እኛ በምንኖርበት ፍጥረተ ዓለማት ጥርቅም (universe) ውስጥ 1,000,000,000 ከፀሐይ የሚበልጡም የሚያንሱም ከዋክብት ይገኛሉ። ለኛ ቅርብ ከሆነው galaxy ከፀሐይ የምትበልጥ ሌላ ፀሐይ አለች፤ ስሟም Alpha Century ይሰኛል። ከሷ የሚመጣው ብርሃን (speed of light 300,000km/sec) መሬት ላይ ለመድረስ 300 ዓመት መጓዝ አለበት። የ Telescopic Observatory Study እስከአሁን እንዳሳየው 1,000,000 galaxy ዎች በህዋ ላይ ተሰራጭተው ይገኛሉ። ርቀታቸው ግን እጅግ ሰፊ ስለሆነ በመደበኛው የርዝመት መለኪያ (km) ለመገንዘብ ያስቸግራል። በዚህም ሳይንቲስቶች Light-Year ን የዓለማት የርቀት መስተጋብርን ለመግለጽ ይጠቀማሉ። 1 Light-Year ከ 9.46 ቢሊዮን km ጋር እኩል ነው።

እዚህ ላይ የምንገነዘበው ሁለት ነገር አለ

1. መሬት እጅግ፣ እጅግ፣ እጅግ ትንሽ አካል መሆኗን እና

2. ሕዋ እጅግ፣ እጅግ፣ እጅግ ሰፊ እና ወሰን አልባ ዓለም እንደሆነ።

ስለዚህ
**ይህን ሁሉ ዓለማት የሚቆጣጠር ፈጣሪ ከህዋዊ ዓለማት የተለቀ እና የገዘፈ መሆን አለበት፣

**ይህን ሁሉ ዓለማት የሚገዛው ፈጣሪ ሃይሉ ወሰን የሌለው መሆን አለበት።

ግን አብዛሃኛው ሃይማኖቶች ላይ ያሉ ፈጣሪዎች

-ሲቆጡ
-ሲያስፈራሩ

-ሲዝቱ
-ኢፍትሐዊ ፍርድ ሲሰጡ

-ሲያዳሉ
-እነሱ ራሳቸው መግደል ሲችሉ ሰው ሰውን ግደል ሲሉ

-ሲራገሙ
-ሲሳደቡ .....እናያለን

በመሠረቱ እነዚህ ነገሮች የሰው ባህሪ ናቸው። ያንን ሁሉ ሕዋዊ ዓለማት የሚገዛ ፈጣሪ በማይረባ ነገር ከተገለፀ ተናጋሪውም እያስተዉል፤ ሰሚውም እያገናዝብ።

ከላይ እንዳየነው የዓለማት ስፋት ከአይምሯችን በላይ ነው። ግን ሃይማኖት የሚጀምረው የኛዋ መሬት ላይ ያውም ትንሿ ፍልስጤም ላይ ነው። አንድ ሰው ካራን ከተማ (ሰሜን ሶርያ) ይኖር ነበር። ከዚያም ወደ ከነዓን (ፍልስጤም) ተሰደደ። የዚህ ሰው ስሙ አብርሃም ይባላል። እንግዲህ አብርሃም የአይሁዶች፣ የክርስቲያኖች እና የሙስሊሞች አባት ብቻ ሳይሆን በ Light-Year ርቀት ላይ ለሚገኙት ለነዚያ ለቢሊዮናት ሕዋዊ ዓለማትም አባት ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ይህ ሃይማኖት ስለሆነ።

ፀሐይ ማታ ማታ የጭቃ አረንቋ ውስጥ ገብታ ታድራለች፤ ጧት ደግሞ ከጭቃ አረንቋው ወጥታ ታበራለች፤ ከታላቁ አሌክሳንደር ውጭ የጭቃውን አረንቋ ቦታ ያየው የለም" የሚለው የሃይማኖት ትምህርትስ ፍቺው እንዴት ነው?

"ሰማዩ መሬቱ ላይ እንዳይወድቅ በአራት ባላ ተደግፎ ተይዟል" የምትለው ሃይማኖታዊ ልቃቂት ዕውቀትስ ማን ይሆን አመስጣሪዋ?"

የሚል ነበር ሰውየው ለልጁ አስተያየት የማይገናኝ ምላሽ የበውቀቱን ጽሑፍ አምጥቶ የሰጠው፡፡ እኔም የምላሹን አለመገናኘት ስመለከት እኔን “መልስ ስጥ!” ለማለት እንደሆነ ገባኝና ለበውቀቱ ይሄንን ልለው ፈለኩ፡-

ይህ ሐሳብ እንጪጭ ነው፡፡ ሲጀመር “...የዚህ ግዙፍ ፍጥረተ ዓለም (ዩኒቨርስ) ፈጣሪ ምን ያህል ሊገዝፍ ሊያይል ሊረቅ ከሰው መረዳት አቅም በላይ እንደሚሆን መገመት ቀላል ነው” ብየ የተናገርኩት ባለፈው ለበውቀቱ ኢአማኒነት መልስ በሰጠሁበት ጽሑፍ ላይ እኔ ነኝ፡፡ ሐሳቡን ከወሰደ አሟልቶ ቢወስድ መልካም በሆነ ነበር፡፡ ይሁንና በውቀቱ ከኢአማኒነት ማለትም ፈጣሪ እግዚአብሔር የለም ከማለት ወደ አማኝነት ማለት “ፈጣሪ እጅግ እጅግ እጅግ ግዚፍ ነው እንጅ አለ!” ወደ ማለት መምጣቱ ትልቅ ለውጥ ነው፡፡

እግዚአብሔር ራሱ ከፈጠረው ፍጥረተ ዓለም (ዩኒቨርስ) እጅግ የገዘፈ ፈጣሪ ሊሆን ቢችልም ሁሉን ቻይ እንደመሆኑ በፈለገው መልኩ መለዋወጥና የእኛ አቅምና ችሎታ በፈቀደልን መጠን እኛ ልንረዳው በምንችለው መልኩ ተገልጦ ከፍጥረቱ ሁሉ አልቆ በአርአያው በአምሳሉ ከፈጠረው ዘፍ. 1፤27 ፍጥረቱ ጋር ግንኙነት መፍጠር እንዳይችል የሚከለክለው የሚገታው የሚያቅበው ነገር እንደሌለና ሊኖርም እንደማይችል መረዳት መገንዘብ ደግሞ ያስፈልጋል፡፡

ምክምያቱም እግዚአብሔር እንደ እግዚአብሔርነቱ ያለው ነገር ሁሉ እንዳለ ሆኖ “ለሰው ልጆች ልገለጥላቸው” ቢል አንደኛ፡- ከግዝፈቱ የተነሣ ይህቺ ዓይናችን ልታየው አትችልም፡፡ ምክንያቱም ዓይናችንን ገልጠን ቀና ብለን ወደሰማይ እንመልከት ብንል የእሱ ፍጥረት ከሆነው ፍጥረተ ዓለም እንኳ እጅግ እጅግ እጅግ በጣም ኢምንቷን እንጅ ሁሉንም የፍጥረተ ዓለም አካል ዓይናችን ጠቅልሎ ሊያይ አይችልምና፡፡ ታዲያ ከፍጥረተ ዓለሙ እንኳ ኢምንቷን ብቻ ለማየት የተገደደ ዓይናችን የዚህን እጅግ በጣም ግዙፍና መጨረሻው የማይታወቅ ፍጥረተ ዓለም ፈጣሪንማ ምኑን ሊመለከት ይችላል?

ሁለተኛ፡- እግዚአብሔር እሳትን ወይም እንደ ፀሐይ ያሉ አቃጣይና ዓይን አፍጥጦ ሊያያቸው የማይችሉ ፍጥረታትን የፈጠረ እሳትና አንደበት ሊገንጠው በማይችል መልኩ እጅግ አቃጣይና ከብርሃኑ ኃያልነት የተነሣም ፈጽሞ ዓይን ሊያየው የማይችል ፈጣሪ እንደመሆኑ መጠን እንዲህ እንደሆነ ቢገለጽልን ፈጽሞ መቋቋም አንችልምና ሊገለጽልን የሚችለው

በአቅማችን በችሎታችን መጠን መሆኑ ግድ ነው፡፡ ስለዚህ ነው እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጸው መልኩ ለእኛ አቅም በተስማማና በሚመጥን መልኩ ከሰው ልጆች ጋር ግንኙነት የፈጠረውና እራሱን የገለጠው፡፡

እግዚአብሔርን በክብሩ፣ በኃያልነቱ፣ በገናናነቱ ማየት ስለማይቻልም ነው እግዚአብሔር ከአዳም ጀምሮ ለነቢያቱ በዘመነ ሥጋዌው ደግሞ ለሐዋርያቱና ለሕዝቡ ሰው ሊረዳው በሚችል መልኩ ተገልጦ ለሰዎች የታየ ከሰዎች ጋር የተገናኘ መሆኑን ቅዱስ ቃሉ የገለጸ ሆኖ እያለ እንደገና ደግሞ "...መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም!" ዮሐ. 1፤18 ሲል መግለጹ፡፡ እግዚአብሔርን በክብሩ፣ በኃያልነቱ፣ በገናናነቱ ማየት ስለማይቻል፡፡

እግዚአብሔርን በክብሩ በኃያልነቱ በገናናነቱ ማየት ከፈለጉ ሰዎች ሊቀ ነቢያት ሙሴ አንዱ ነበር "...እባክህ ክብርህን አሳየኝ አለ። እግዚአብሔርም እኔ መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ፤ የእግዚአብሔርንም ስም በፊትህ አውጃለሁ፤ ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ፥ የምምረውንም እምራለሁ አለ። ደግሞም። ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ" ዘጸ. 33፤19

ለቀሪው በውቀቱ አጣሞና አሳስቶ ላነሣው ጥያቄ ማለትም እግዚአብሔር ሰዋዊ አምላክ (personal God) ሳይሆን ለእኛ ግን የሆነ መስሎ የቀረበበትን ምክንያት በወቅቱ "ለበውቀቱ ደጋፊዎች መልስ!" ብየ አስከትየ በጻፍኩት ጽሑፍ ላይ በደንብ አብራርቸ የገለጥኩት በመሆኑ ሰዉ ሊረዳ ባልቻለ ቁጥር ሽህ ጊዜ መደጋገም አልችልምና አሁን እዚህ ላይ አልደግመውም፡፡ እስኪገባቸው ድረስ ያንኑ ደጋግመው ያንብቡት፡፡

ሡዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com

http://www.ethiopanorama.com